# ለማንም ተሸጠሽ ስልጣን ላይ ተመለሽ

በልጅግ አሊ

ጠላይን የማታውቁት እንደምትኖሩ የታወቀ ነው ። ያ ቦታ የተመሰረተው የብሄራዊ ውትድርና ለማሰልጠን ነው።ቁም ነገሩ ግን ለሁላችንም አደለም። እንዳፈጣጠራችን እኛ አገርን ለመጠበቅ እነርሱም እኛ በሞትላት አገር ለመንደላቀቅ ሲሉ የፈጠሩት የብሔራዊ ወትድርና ማሰልጠኛ ቦታ ነው ።እኛ ታፍስን እነርሱ አፍሰውን እኛ ሞተን እነርሱ ገለውን ብዙ ዘመን ስለኖርንና ብዙው ታሪካችን ስላልተፃፈ ዛሬ ሲነገር እውነቱ ውሸት ውሸቱ እውነት ይመስላል።ሀቁ ግን የፓለቲካ አቋማችን እየታየ ለአብዮቱ የማንጠቅመው ወይም የሚጠቅም ዘመድ የለለን የምንመደብበት ቦታ ነበር።

ከቀይ ሽብር ተርፈን የነበርነው እንደምናስታውሰው ከሆነ ከእስር ቤት ከተፈታን በሁላ እንዳንሞት እንዳንተርፍ ተደርጎ በልዩ ልዩ ሕጎች መብታችንን አጥተን በገዛ አገራችንን መኖር ስለተፈቀደልን እንድናመሰግን እየተነገረን ለብዙ አመታት ከሞቱት በላይ ከቆሙት በታች ተደርገን እንደነበርን የማይዘነጋ ነው ። ከሁሉም የሚብሰው ለትምህርትም ሆነ ለስራ የድጋፍ ወረቀት ማግኘት ነው።ያቆሸሻችሁትን የአብዮት ሸማ እንድታጥቡ እየተባልን ከምንችለው በላይ ግፍ እየተቀበልን ከማንኛውም ጥቅም ተገለን ሌሎቹ ግን ሁሉን ለራሳቸው ሲያግበሰብሱ የከረሙ እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

በትምህርት ችሎታ ሳይሆን በድጋፍ ወረቀት ብዛትና በኢሰፓ ግንኙኝት በየውጩ ለመማር የመጡት ቁጥር ብዙ መሆኑን የሚክድ የለም ።ይህ እድል ደግሞ ለኛ እነርሱ ባወጡት እኛን እንዳንማር ፣ እንደንሰራ፣ እንዳንበላ በሚያደርግ ህግ ተቀፍድደን መኖራችን የሚዘነጋ አደለም። ከሞት ከተረፈው ውስጥ ለመማር እድል ያገኘው በጣም ጥቂት ነበር፡፡ ለነገሩማ በዛ ክፉ ዘመን በማትሪክ ውጤት ከርቸሌ አንደኛ መውጣቱ በኢሕአፓ ውስጥ የነበርነው በችሎታ ምን ያህል እንደምንበልጣቸው ያሳያል።ካለ አስተማሪ ፣ ካለ መፀሀፍ ፣ በእስር ቤት ውስጥ ሆነን፣ በሃገሪቱ ውስጥ ከታወቁት ትምህርት ቤቶች መብለጣችን ግልፅ ነው። ይህንን ሰው ምን ነካው ምንድነው የሚያወራው ልትሉ ትችሉ ይሆናል ። ስለዚህ ጉዳይ የትም የተፃፈ አላነበብኩም።እኔ በበኩሌ ይህ የተካኼደው የግፍ ስርአት ጠቅላላ የህብረተሰባችን አመሰራረትና የትምህርተ ክፍፍል አበላሽቶት፣ ሆዳምነት አስፍቶ ፣ እንዴት እንደሄደ ለመግለጽ እሞክርለሁ ።ብዙ ሰዎች ደግሞ በዚህ ሁኔታ ምን ያህል እንደተጎዱ ማወቅ ያስፈልጋል ።የተጠቀሙት ቁጥርም ቢሆን ትንሽ አደለም።

እኛ በዚያ ግዜ "ያቆሸሽነውን" የአብዮትን ሻማ ስናጥብ እነርሱ ደግሞ አብዮቱ ፍሬ ሲለቅሙ፣ ሲጠቀሙ ነበር ። የውጭ ትምህርትም ከዚሁ ጋር በተያየዘ አፈፃፀሙ በድጋፍ ወረቀት እንደነበር የሚረሳ አልነበረም ። የጀነራል ልጀ በህንድ ወይም ምስራቅ ጀርመን ፣ የኮነሬል ደግሞ ቼክ ፣ የሻለቃ ቡልጌሪያ ፣ የሻንበል ራሻያ ፣ የመቶአለቃ ደግሞ ኩባ እንደሚመደቡ ሲታወቅ እኛ ግን ድጋፍ ወረቀት የማይጠየቅበት ጠላይ ብሔራዊ ውትድርና ማሰልጠኛ ወይም ታጠቅ፣የድጎማ አስተማሪ ፣ ማለትም በወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው ፕሮግራም ወይም ደግሞ የደርግ አፍቃሪዎች የማይፈልጉት ቦታ ነበር የተመደብነው ። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ከተገኘው የትምህርት እድል ውስጥ ግማሹ ለኢሰፓ ስለሚሰጥ አባላቱ ይህንን ጥቅም ለማግኘት የትምህርት ደረጃ እንደማይጠየቁ የታወቀ ነው።በዚህም ምክንያት የደርግ የመጨረሻ ሰሞን አካባቢ ጀርባውን የከበደው የደርግ ካድሬ ሁላ እስኪለይለት ድረስ ሄጄ ምስራቅ አውሮፓ ልቀመጥ ብሎ ሰቅስቆ እንደወጣ የታወቀ ነበር።

ደርግ ወርዶ ወያኔ ሲተካ ይህ የድጋፍ ወረቀት ሰልፈኛ ወደ ምዕራቡ ፈለሰ። ፈልሶም በሰበሰበው ልምድ ወዲያውኑ የፓለቲካ ድርጅት እያቋቋመ እንደገና ለጥገኝነት የሚጠቅም የድጋፍ ወረቀት እየሸጠ ተቀመጠ ። የአለፈውን ቂሙን ባለመርሳት ፀረ ኢሕአፓነቱን ተያያዘው።

ዛሬ ታዲያ እነርዚህ የድጋፍ ወረቀት አርበኞች ፀረ ኢሕአፓ ቢሆኑ ምን ሊደንቀን ።ባለፉት ፅሁፎቼ ውስጥ የደደቦች ሸንጎ አጋፋሪዎች የትምህርት ደረጃ ምን እንደሚመስል ጠቅሻለሁ ። ሕልማቸው ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ አገር ቤት ተመልሰው እኛ ከሻቢያ ከወያኔ ተዋግተን ነፃነትዋን ያሰጠበቅነትን አገር መምራት ነበር ። ግን ሳያስቡት ቆራጡ መሪያቸው ስለጠፋ ግራ ተጋብተው በየሞስኮው የፓለቲካ ትምህርት ቤት ለቅሶ እንደደተደረሳቸው ግልፅ ነው፡፡

ስሞኑን ደግሞ ኢትዮጵያን ለሻቢያ ለምን አልሸጣችሁም በማለት ነጋ ጠባ ከኢሕአፓ ላይ ሊወርዱ አልቻሉም ። በደደቦቹ ተረት

# „ለማንም ተሸጠሽ ስልጣን ላይ ተመለሽ“

ካሁን ወዲያ እንደማይሰራ ማወቅ እስከሚሳናቸው ድረስ ታውረዋል ።

ዛሬ ኢሕአፓ የሚፈሩት ነግ ተነገ ወዲያ በሃገር ቤት ያለው ጭፍጨፋን አሽንፎ ሲወጣ ሊያመጣ የሚችለውም ሀይል ስለሚያውቁት ከወዲሁ ኢሕአፓን ለማጥፋት ትግሉን ጀምረውታል። የኢሕአፓ አባላት ከየስደቱ ፣ ከየድኅማ አስተማሪነቱ ፣ ከወታደርነቱ ፣ ማለትም ድጋፍ ወረቀት የማያስፈልግበት ቦታ ላይ ተጥለው ከነበሩነበት በአንድነት ከተነሱ ብዙ ቀም ነገሮች ሊፈፅሙ እንደሚችሉ እሙን ነው ። የድጋፍ ወረቀት ቦታ እንደማይኖረውና የኢሰፓ ካድሬዎችም ሆኑ የወያኔ ባለስልጣን የሆኑት ፣ ከነርሱም ጋር ቢወዳድረው እንደማይሳካላቸው እሙን ነው ። ያለውን የኢሕአፓ ሀይልን ያውቁታል ፡ ይፈሩታል ፣ እንቅልፋቸውን ይነሳቸዋል ፡ ያቃዣቸዋል ። ስለዚህም ነው ከሻቢያ ከወያኔ ወይም ከኦ ኤል ኤፍ ማበር የሚሻላቸው ። አገር ትዳን ትጥፋም ካሁኑ የስልጣን ቀብድ ካልተሰጠን አንስማማም ብለው ነው የሚያምኑት።

ለነገሩ ታሪኩን አመጣሁት እንጂ በአሁኑ ጊዜ ጠላታችን ደርግ ሳይሆን ወያኔ ነው ።አገራችንም አደጋ ላይ ነች ። የቀድሞ ታሪካችንን እያነሳን መጣላታችን የሚጠቅመው ወያኔን ነው። ይህም ሲባል ደግሞ ለህብረት ሲባል ውነቱ ተደብቆ ይለፍ ማለት አይቻልም ። በየተደጋጋሚው ኢሕአፓን ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት ሊቆም ይገባል እላለሁ ። ማጥፋትስ ይቻላል ወይ? ብሎ መጠየቅም ተገቢ ነው ። በየፓልቶኩ ላይ ምኞትን መናግር ኢሕአፓን አያጠፋውም ። የተቀነባበረው ቀይ ሽብር ብዙ ጎዳው እንጂ አላጠፋውም ። የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች ስለህብረት ሲናገሩ እንደምንሰማው ከሆነ ለህብረት መቆም አሰፈላጊ እንደሆነ ነው የሚገልፁልን ። ከሆነ ዘንዳ አባሎቻቸውን በውስጥ ስድቡን እንዲቀጥሉ መገፋፋት የለባቸውም ። ስድቡ ኢሕአፓን ይጎዳዋል ማለቴ ሳይሆን ክፍፍሉ ወያኔን ይጠቅመዋል ነው ።

ለማንኛውም ኢሕአፓ ሲረግሙት ስለሚበዛ እናጠፋዋልን ያላችሁት ደርጅት ስሞኑን ጥራት ባለው ሁኔታ በየፓልቶኩ እየቀረቡላችሁ ስለሆነ ከስድቡ በመቆጠብ እና ስነስርአት በመያዝ የጭንቅላታችሁ ሁኔታ በፈቀደው፣ የየካቲት ስልሳ ስድስት የፖለቲካ

ትምህርት ቤት ፕሮፖጋንዳ ትታቸው በገንቢው ውይይት ላይ ብትሰለፉ ብዙ ትምህርት እንደምታገኙ ጥርጥር የለኝም ። ወደፊት ለምትመሰረተው ኢትዮጵያ በቂ ሆናችሁ የምትገኙት በዚሁ መንገድ ብቻ ነው።

ለዛሬ ስለሃገራችን የሚያስብ ሁሉ በስላም ይክረም!!!

በልጅግ አሊ